?? ????? ?? ? ???? ? ????

# ልሳነ ህግጋዘጣ

**Benishanigul Gumuze Regional State**

# LISSANE HIG GAZETA

23 ኛ ዓመት ቁጥር 144
የካቲት /2009

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ
ክልላዊመንግሥት ክልል ምክር
ቤትጠባቂነት የወጣ አዋጅ

23th Year No 144
February /2017


---

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ.ም እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 144/2009ዓ.ም

## አዋጅ ቁጥር 144/2009 ዓ.ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ.ም እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 144/2009ዓ.ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አከካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ.ም እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

ለአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ሕጋዊ አሰራር ተከትሎ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑና ባልተማከለ አስተዳደር መርህ መሠረት በማድረግ የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚያደርጓቸውን ጥረቶች ለማገዝ፤

በአዋጁ ቀበሌ ይገባናል ጥያቄ ለማስተነገድ የተደነገጉ መስፈርቶች መንግስት በአሁኑ ወቅት ለሚቀርቡ የህዝብ የመልካም አስተዳደር እና የመንግስት አገልግሎት ተደራሽነት ጥያቄ በሕግ በአግባቡ ማስተናገድ እንዲቻልና ለዚህ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩ ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተሻሻለው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ ቁጥር 3.1 መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### አንቀጽ 1

### አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ *"የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 እንደገና ማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር--/2009 ዓ.ም (ማሻሻያ)"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላላል፡፡

### አንቀጽ 2

### ማሻሻያ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ.ም አንቀጽ 11 ንዑስ  አንቀጽ 2 ፊደል ተራ “ሐ” እንደሚከተለዉ ተጨምሯል፡፡

“ ሐ/ በአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ  አንቀጽ 2 ፊደል ተራ “ሀ” ላይ የተደነገገዉ የህዝብ ብዛት መስፈርትን ቢኖርም የክልሉ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በልዩ ሁኔታ የአካባቢው መልከዓምድራዊ አቀማመጥ ምቹነት ለመፍጠር፣የኅዝብ አሰፋፈር፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት እና በጥናት በመለየት አይቶ ሲቀርብ የክልሉ ምክር ቤት በተጨማሪ ቀበሌ አስተዳደሮችን  ሊሰይምና ሊያቋቁም ይችላል ፡፡ ”

<u>**አንቀጽ 3**</u>

ይህ አዋጅ በልሳነ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል

አሶሳ

-------ቀን 2009 ዓ/ም

አሻድሊ ሃሰን አልአጀብ

የቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ፐሬዝዳንት